በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ከጁን 21-30 የነበረው የአየር ሁኔታ ግምገማ እንዲሁም

ከጁላይ 1-10 እና ከጁላይ 11-20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ጁላይ 2025

አዲስ አበባ

1. እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይም በመጨረሻዎቹ ሰባት ቀናት ላይ በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በጎሬ 43.9፣ 21፣ ጂማ 22፣50፣ ነቀምቴ 71፣ 27.2፣ አዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 30.8፣ አዴት 20.4፣ አይራ 31.4፣ አንገር ጉትን 25.6፣ 36.4፣ አርጆ 20.2፣ 22.8፣ አይከል 23.4፣ በደሌ 46.4፣ 37.8፣ ብላቴ 36.5፣ 27.2፣ ቦሬ 24.8፣ በሂ 32.8፣ 35.3፣ ቡለን 20.3፣ 30.3፣ 20.8፣ ቻግኒ 21.6፣ ጨዋቃ 26.3፣ 24.2፣ 26.7፣ 26.6፣ ጭራ 49.9፣ 22፣ ዳንግላ 66፣ ደባርቅ 21.3፣ ደብረ ታቦር 31.7፣ ደምቢ ዶሎ 28.8፣ 33.5፣ ኢጃጂ 26.6፣ 25.7፣ 30.8፣ ፉኙዶ 40፣ ጋምቤላ 26.6፣ 24.4፣ 22.4፣ 20.4፣ ጋቲራ 28.8፣ ወሊሶ 43.2፣ ጊዳ አያና 42፣ 26.4፣ ጊምቢ 34.7፣ 35.9፣ 21.3፣ እምድብር 24፣ 21.2፣ ጅንካ 60.7፣ 38.8፣ ካቺሴ 30፣ 62.3፣ ቁሉምሳ 31.5፣ ሊሙገነት 60፣ 23.8፣ ማሻ 30፣ ነጆ 25.5፣ ፓዌ 26.7፣ ሰኮሩ 23፣ 24.4፣ ተርጫ 23.2፣ ወላይታ ሶዶ 22.2፣ የትኖራ 21.5፣ አቦ ሞሪጋ 32.2፣ 37.2፣ 25.6፣ እብናት 32.4፣ ኖፓ 25.8፣ ኦሞ ናዳ 26.6፣ ጊናግር 22.4፣ ሙጊ 27.6፣ ፊንጫ 22.7 እንዲሁም ሸንዲ 20.5፣ 26 ሚ.ሜ የሚደርስ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት በ27 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1)፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የምዕራብና የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40.0 እስከ 71 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ነቀምት፣ ዳንግላ፣ ካቺሴ፣ ጂንካ፣ ሊሙ ገነት፣ ጅማ፣ ጭራ፣ በደሌ፣ ጎሬ፣ ወሊሶ፣ ፉኙንዶ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et



ምስል፡1 ከጁን 21-30 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ሰሜን፣ ምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ የመካከለኛዉ፣ የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ ሰሜን፣ ምስራቅና ምዕራብ ጎጃም፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ ከ21-155 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡



ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከኦሮሚያ ክልል ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ቦረና እና ምስራቅ ቦረና፣ ምዕራብና የደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የምዕራብና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ ዋግ ህምራ፣ የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ኮንታ፣ ዳዉሮ፣ ከፋ፣ ሸካ፣ ቤንች ሸኮ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ የሀዲያ፣ ስልጤ፣ የከንባታ፣ የሃላባ፣ የም ዞኖች፣ ቀቤና፣ ማረቆ፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ ዞኖች፣ አዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡

በሌላ በኩል በሰመራ፣ በገዋኔ፣ በመተሃራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ መተሃራ፣ ድሬ ዳዋ፣ ሸዋ ሮቢት፣ መተማ፣ ፉኙዶ፣ ቀበሪዳሀር፣ ጨፋ፣ ጎዴ፣ ኑራ ኤራ፣ ማጀቴ፣ መኢሶ፣ ባቲ፣ ጋምቤላ፣ አቦምሳ፣ አቦቦ፣ አዳማ፣ ኮምቦልቻ፣ ሽርቀሌ፣ ስሪንቃ፣ ፓዌ እና ቴፒ፣ አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 32.4 እስከ 41.5 ዲግሪ ሴልሸየስ ተመዝግቧል፡፡



ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 ድረስ ዝናብ የዘነባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.2 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁን ወር ሶስተኛው አስር ቀናት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ፣ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት በአብዛኛው የመኸር ሰብል አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች ላይ ነበራቸው፡፡ ይህም የእርጥበት ሁኔታ አስቀድመው ለተዘሩና በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የበልግም ሆነ የረጅም ጊዜ የመኸር ሰብሎችም ለተለያዩ የቋሚ ተክሎችና የጓሮ አትክልቶች የውሀ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንፃር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረዉ፡፡ በአንጻሩ ግን በተጨማሪ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ በጥቂት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የነበረው አንስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አዎንታዊ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ ባሳለፍናቸው ቀናት ከነበረው ተከታታይ ዝናብ ጋር ተዳምሮ በአንዳንደ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛት የተስተዋለ ቢሆንም በግብርናዉ አንቅስቃሴ ላይ የጎላ አሉታዊ ተጸዕኖ አልነበረዉም (ካርታ 4) ፡፡



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

1.3 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት አስር ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛ እና ታችኛው ተከዜ፣ በላይኛው እና ታችኛው አዋሽ፣ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው እና መካከለኛ ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገጸ ምደር የውኃ ፍሰት ነበራቸው (ካርታ 5)፡፡ በተጨማሪም በመካከለኛው አባይ፣ በላይኛው እና በመካከለኛው ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ባሮ አኮቦ እንዲሁም በመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ በጣም ከፍተኛ የሆነ የውኃ ፍሰት እንደነበራቸው የተተነተኑ የውሃ ሚትዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በአንጻሩ በአብዛኛው ዋቢ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ ገናሌ ዳዋ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ መረብ ጋሽ እና የላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች በአብዛኛው ዝቅተኛ እርጥበትና ከፍተኛ ትነት ነበራቸው (ካርታ 5) ።



ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጁን 21 እስከ 30/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

2. መግቢያ

በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ ቀደም ብሎ በደቡብ ምዕራብ እና በምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጀምር ሲሆን፤ በሂደትም እየተጠናከሩ ከሚሄዱ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ጋር ተያይዞ በጁን ወር ውስጥ የተቀሩትን የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ሙሉ በሙሉ ያዳርሳል፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ወር የክረምት ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋ እና እየተጠናከረ የሚሄድበት ጊዜ ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የተሻለ ዝናብ መጠንና ስርጭት ይስተዋላል። በወሩ በመደበኛው ሁኔታ የሚጠበቀው አማካይ የዝናብ መጠን በደቡብ ምዕራብ፣ በምዕራብ እና በሰሜን ምዕራብ ስፍራዎች ላይ ከ200-500 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ18-27 ቀናት ያህል ይዘንባል። በሌላ በኩል በመካከለኛው፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ አካባቢዎች ላይ የወሩ አማካይ የዝናብ መጠን ከ60-200ሚ.ሜ የሚደረስ ዝናብ ከ6-21 ቀናት ያህል ይዘንባል፡፡ ከክረምት ወቅት ዝናብ ድርሻ አኳያ በጁላይ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ30 እስከ 50% የሚሆነውን የወቅቱን የዝናብ ድርሻ ያገኛሉ።

በመደበኛ ሁኔታ የጁላይ የመጀመሪያዉው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ምዕራብ መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

2.1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ይበልጥ እየተስፋፉና እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛው እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የሚኖራቸው ሲሆንና፤ በጥቂት ስፍራዎቻቸው ላይ ደግሞ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6 እና 7)፡፡



ካርታ 6 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

2.2 የሚኖረው የዝናብ ሁኔታ

በሚቀጥሉት ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ ከባድ (ከ1-30 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን ምስራቅ እና በመካከለኛዉ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 8)፡፡



ካርታ 8 ኢ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2025
የሚኖረዉ ከፍተኛ የዝናብ መጠን

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት ቀናቶች ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና የሚያገኙት የዝናብ መጠን

ክልል	ዞን	የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን
አሮሚያ	ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ምዕራብ አርሲ እና አርሲ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ምስራቅ ቦረና	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ)
አማራ	የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ፣ የሰሜን፣ ምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ትግራይ	የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ቤንሻንጉል ጉምዝ	ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ጋምቤላ	አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ)
ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ	ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
ሲዳማ ክልል	ሁሉም የክልሉ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1 እስከ 10 ሚ.ሜ)
አዲስ አበባ፣ ድሬዳዋ እና ሐረሪ		ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
አፋር	ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሀሪና ጋቢ ዞኖች	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1 እስከ 29 ሚ.ሜ)
ደቡብ ኢትዮጵያ	ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ባስኬቶ፣ ጌድዮ፣	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ)
	አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)
ሶማሌ	ሲቲ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ጃረር፣ ነጎብ፣ ሊበን እና ዳዋ፣ ዞኖች	ቀላል መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ)

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.3 የሚኖረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት ሁኔታ

በጁላይ የመጀመሪያው አስር ቀናት ከሚኖረው ከፍተኛ የፀሐይ ሀይል ጋር በተያያዘ በተለይም የቀኑ ከፍተኛ ሙቀት በአፋር ክልል፣ በምስራቅ አማራ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ ሥፍራዎች ሊይ ከ26 እስከ 41 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን አሃዛዊ ትንበያዎች ያመላክታሉ (ካርታ 9)፡፡



ካርታ 9 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 1-10, 2025 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

2.4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 11 እስከ 20/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች በሁሉም የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎችን የሚያዳርስበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚሁ ጋር በተያያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ነጎድጓዳማ እና ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይዘወተራል፡፡

በመጪዎቹ የጁላይ ሁለተኛው አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የዝናብ መጠንና ሥርጭት እንደሚኖራቸው የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10)። ከዚሁ ጋር በተያዘም በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የአሀዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 10)፡፡ በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡



ካርታ 10 እ.ኤ.አ. ከጁላይ 11-20, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

2.5 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው እርጥበት ይኖራቸዋል። ይህም ሁኔታ የሚኖረው እርጥበት ለወቅቱ የግብርና ስራ እንቅሥቃሴ በአመዛኙ አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ቢሆንም፤ ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስና የሚኖሩትን መልካም አጋጣሚዎች በላቀ ሁኔታ ለመጠቀም የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በሁሉም ደረጃ በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

ዞኖች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የተሰጠ ምክረ ሃሳብ
የክረምት እርጥበት ተጠቃሚ የመኸር አምራች ዞኖች				
ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ ፣ የሰሜን፣ ፣ መካከለኛዉ ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የአዊ ዞኖች ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች ፣ አኝዋክ፣ መዥንግ፣ የኑዌር እና የኢታንግ ልዩ ወረዳ ፣ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	የአፈር ወስጥ እርጥበት መሻሻል ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገትና የአጭር ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት	የአፈር እርጥበት መብዛት፣ ውሃ ገብ በሆኑና በወንዝ ዳርቻ ባሉ ሰብሎች ላይ የአፈር መታጠብ የአረም መስፋፋት	የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም ዘር መዝራት የውሃ ማንጣፊፍያ እና የጎርፍ መቀልበሻ ቦዮችን ከወዲሁ ማዘጋጀት የማዳበሪያ አጠቃቀምን በትክክለኛው ሰዓት መተግበር የእርሻ ድግግሞሽን መቀነስ
ዋግ ህምራ፣ ሰሜን እና የደቡብ ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ የመካከለኛዉ፣ የደቡብ ምስራቅ	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን	ለመኸር እርሻ ስራ እንቅስቃሴ ለማከናወን	ከፍተኛ ትነት በሚኖርባቸዉ አካባቢዎች መጠነኛ የሆነ	የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የማሳ ዝግጅትና ዘር ማከናወን

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ትግራይ ዞኖች፣ ቀልበቲ፣ ፈንቲ፣ አውሲ፣ ማሂ፣ ሀሪና ጋቢ ዞኖች	ያለዉ እርጥበት	ለረጅም ጊዜ ሰብሎች እድገት የመጠጥ ውሃና የግጦሽ ሳር አቅርቦት መሻሻል ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት	የአፈር ዉስጥ እርጥበት መኖር	የእርጥበት እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች የአፈርና የውሃ እቀባ ስራ ማከናወን የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል
በልግ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውና የመኸር አብቃይ የሆኑ ዞኖች				
የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ባስኬቶ፣ ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ	ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት	ቀድመው ለተዘሩ ለረጅም ጊዜ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም	ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውሃ በማሳዎች ላይ መተኛት የአፈር መሸርሸር የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት	ረባዳማ በሆኑ ማሳዎች ላይ የእርጥበት መብዛት እና ውሃ በሰብሎች ላይ መተኛትን ሊያስከትሉ ስለሚችሉ ይህንን ለመከላከል የሚያስችሉ የውሃ ማንጣፈፍ ስራዎችን መስራት • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን በየጣልቃው የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ
የደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት	ለመኸር ግብርና እንቅስቃሴ የማሳ ዝግጅትና ዘር ለመዝራት ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል	ከፍተኛ ትነት መኖር የደረሱ የበልግ ሰብሎች በእርጥበት መጎዳት	የሚገኘውን እርጥበት በመጠቀም የመኸር የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ማከናወን የአፈርና የውሃ እቀባ ማከናወን • የደረሱ የበልግ ሰብሎችን የሚኖሩ ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ
በልግ ዋነኛ የዝናብ ወቅታቸዉ የሆኑ ዞኖች				
ምዕራብ ጉጂ እና ጉጂ ፣ ምስራቅ ቦረና፣ አሪ፣ ኮንሶ፣ ቡርጂ፣ አሌ፣ ጋርዱላ፣ ኮሬ እና ደቡብ ኦሞ ዞኖች ፣ ፋፈን፣ ኤረር፣ ነጎብ፣	ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን	ለተዘሩ ሰብሎች ፍሬ ለማፍራት	ከፍተኛ ትነት መኖር ደረቅ ሰሞናት መኖር	የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል የደረሱ የበልግ ሰብሎችን የሚኖሩ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ሲቲ፣ ጃረር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች	ያለዉ እርጥበት	የዝናብ ውሃ ለማሰባሰብና ለማጠራቀም • ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት	• የሚኖረው እርጥበት በመድረስ ላይ ላሉ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን	ደረቅ ቀናቶች በመጠቀም መሰብሰብ

2.6 እ.ኤ.አ ከጁላይ 1 እስከ 10/2025 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገራችን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። ሆኖም ግን አልፎ አልፎ ከሚኖረው ተደጋጋሚ የሆነ ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ የከተማም ሆነ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የወንዞች ከፍታ መጨመር ሊያስከትል ይችላል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የጎረፍ ስጋትን ለመቀነስም ሆነ መልካም ዕድሎችን ለመጠቀም የሚከተሉት ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቢች ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሃዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

የውኃ ተፋሰሶች	የእርጥበት ሁኔታ	አዎንታዊ ተጽዕኖ	አሉታዊ ተጽዕኖ	የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ
በአብዛኛው • ተከዜ • መረብጋሽ • አባይ • ባሮ አኮቦ • የላይኛው እና የመካከለኛ • ኦሞ ጊቤ • ስምጥ ሸለቆ	ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት	• የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት መሻሻል • የከርሰ ምድር የውኃ መጠን መሻሻል • የመስኖም ሆነ የሃይል ማመንጫ ግድቦች ውኃ መጠን መሻሻል	• ቅፅበታዊ ጎረፍ መከሰት • የወንዞች ከልካቸው በላይ መሙላት • የደለል ስጋት መጨመር • የመንገዶች በውኃ መጥለቀለቅና •	• የጎርፍ የፍሳሽ መውረጃዎች ቦዮችን ማፅዳት • የጎርፍ መቀለበሻ ቦዮችን ማዘጋጀት • የዝናብ ውኃ ማሰባሰብና ማጠራቀም • የጎርፍ ተጽዕኖ ትንበያዎችንና ምክረ

ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

አዋሽ		• በሁሉም አካባቢ የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን መሻሻል		ሀሳቦችን በየጊዜው መከታተል
በአብዛኛው የመካከለኛው እና የታችኛው • አዋሽ • አፋር ደናክል • ገናሌ ደዋ • ዋቤሸበሌ ኦጋዴን	ከመጠነኛ እስከ ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ	• የጎርፍም ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር	• ከፍተኛ ትነት • ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት • ዝቅተኛ የውኃ ፍሰት • እርጥበት አጠር በሆኑ አካባቢዎች የውሃ እጥረት • የገጸ ምድር የውኃ ፍሰት መቀነስ • የተፈጥሮም ሆነ የሰው ሰራሽ የውኃ ማጠራቀሚያዎች የውኃ መጠን መቀነስ • የከርሰ ምድር የውሃ ሃብት መቀነስ	• የሚገኘውን የዝናብ ውሀ ከብክነት እና ከብክለት በመከላከል መጠቀም • ወራጅ የዝናብ ውሀን ማሰባሰብና ማጠራቀም • ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም • የውሀ እጥረት በሚገጥማቸው አካባቦዎች የውኃ ተደራሽነትን ማረጋገጥ • የሚገኘውን ውሀ በቁጠባና ውጤታማ በሆነ ሁኔታ ማስተዳደር • የገጸ ምድር የውሀ ሀብትን በአግባቡ መጠቀም

Ethiopian Meteorology Institute

ስልክ+2511155383946ፋክስ 0115517066 ኢ.ሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et